ተቀባይነት ያለው ጥገኝነት አጭር ምልከታ

ከUSCIS የታሪክ ቢሮ እና ቤተ መጻሕፍት የተገኘ

ስድስተኛ እርምጃ፡- የጥገኝነት ሠራተኛው የብቁነት ማረጋገጫ ያከናውናል እንዲሁም ውሳኔውን ተቆጣጣሪ የጥገኝነት ሠራተኛው ይገመግማል፡-

የጥገኝነት ሠራተኛው አመልካቹ በጥገኝነት እና ዜግነት ህጉ (INA) አንቀጽ 101(a)(42)(A) መሠረት የስደተኝነትን ትርጓሜ የሚያሟላ መሆኑን እና በጥገኝነት እና ዜግነት ህጉ (INA) አንቀጽ 208 (b)(2) ውስጥ ያለው ጥገኝነት ላለማግኘት የተቀመጠው እገዳ የሚመለከተው መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ተቆጣጣሪ የጥገኝነት ሠራተኛው ከህጉ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ለማረጋገጥ የጥገኝነት ሠራተኛውን ውሳኔ ይገመግማል፡፡

ሰባተኛ እርምጃ፡- ማመልከቻው ውሳኔ ያገኛል

አብዛኛውን ጊዜ ቃለ-መጠይቁ ከተደረገ ከሁለት ሳምንታት በኋላ አመልካቹ ውሳኔውን ለመቀበል ወደ ጥገኝነት ቢሮው ተመልሶ ይሄዳል፡፡ በአጠቃላይ ማመልከቻው ከገባበት ቀን ከ60 ቀን በኋላ አመልካቹ ውሳኔውን ይቀበላል፡፡ ሆኖም በሂደት ላይ ባሉ የደህንነት ወይም የኋለኛ ታሪክ ምርመራዎች የተነሳ ለባለጉዳዮች የሚሰጡ ውሳኔዎች ሊዘገዩ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ተቀባይነት ባለው ሁኔታ ውስጥ ለሚገኝ፣ በዲስትሪክት ቢሮ ቃለ-መጠይቅ ለተደረገለት ወይንም ጉዳዩ በጥገኝነት ክፍል ዋና ቢሮ ሠራተኛ በመታየት ላይ ለሚገኝ አመልካች ረዘም ያለ የማስፈጸሚያ ጊዜ ሊያስፈልግ ይችላል፡፡ እንዲህ ባሉት ሁኔታዎች ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ውሳኔው ለአመልካቹ በፖስታ ይላክለታል፡፡

ተጨማሪ የመረጃ ምንጮች



በጥገኝነት ቃለ-መጠይቅ ወቅት የዩናይትድ ስቴትስ መንግስትን ምንም አይነት ወጪ ሳያስወጡ የራስዎን የህግ አማካሪ ይዘው የመቅረብ መብት አለዎት፡፡ ድጋፍ ሊሰጡዎት የሚችሉ በነጻ ወይንም በቅናሽ ዋጋ አገልግሎት የሚሰጡ የህግ አማካሪዎችን ወይም ማህበረሰብን መሠረት ያደረጉ ለትርፍ የማይሰሩ ድርጅቶችን ማግኘት ይችላሉ፡-

- ነጻ የህግ አገልግሎትን በተመለከተ መረጃ የሚሰጠውን ድረ-ገጻችንን መመልከት፡፡
- በ**1-800-870-3676** ወደ ቅጽ መጠየቂያው መስመር መደወል፡፡
- ወደ ዩናይትድ ስቴትስ የፍትህ መምሪያ የስደተኞች ጉዳይ ስራ አስፈጻሚ ቢሮ መሄድ፡፡

  http://www.usdoj.gov/eoir. የተሰኘውን ድረ-ገጽ ይመልከቱ
- በቤትዎ አቅራቢያ የሚገኘውን የጥገኝነት ቢሮ ወይንም የዲስትሪክት ቢሮ ማነጋር፡፡

የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽን (ዩ.ኤን.ኤች.ሲ.አር.) ተወካዮች የ I-589 ፎርምዎን በመሙላት ሊረዱዎት ይችሉ ይሆናል፡፡ ዩ.ኤን.ኤች.ሲ.አርን ለማነጋገር በ **(202) 296-5191** ይደውሉ ወይም **http://www.unhcr.org** ን ይጎብኙ፡፡

በዚህ በራሪ ወረቀት ውስጥ ውይይት የተደረገባቸውን ርዕሰ ጉዳዮች በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎ የሚከተለውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡-

http://www.uscis.gov/asylum
ወይምበ1-800-375-5283 ይደውሉ

M-756 (09/2012) N

ከለላ • ታማኝነት • አገልግሎት

የUSCIS የጥገኝነት መርሀ-ግብር

ለእጩ የጥገኝነት አመልካቾች የተዘጋጀ የመረጃ ሰነድ

U.S. Citizenship and Immigration Services

የጥገኝነት አሰጣጥ ሂደት በአጭሩ

ከዘራቸው፣ ከሀይማኖታቸው፣ ከዜግነታቸው፣ የአንድ ማህበራዊ ቡድን አባል ከመሆናቸው ወይንም ከፖለቲካዊ አመለካከታቸው ጋር በተያያዘ በደረሰባቸው ወይም ይደርስብናል ብለው በሚሰጉት ስቃይ እና እንግልት የተነሳ የተለያዩ ሰዎች በየአመቱ ከለላ ፈልገው ወደ አሜሪካ ይመጣሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ለጥገኝነት ብቁ የሚሆኑት ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ እንዲቆዩ ይፈቀድላቸዋል፡፡

ጥገኝነት ምንድን ነው?

ጥገኝነት ማለት አንድ ብቁ ሆኖ የተገኘ ስደተኛ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ እንዲቆይ እና በሂደት ህጋዊ ቋሚ ነዋሪ እንዲሆን የሚያስችል፤ ስቃይ እና እንግልት ይደርስብኛል ብሎ ወደሚሰጋበት ሀገር እንዳይመለስ የሚሰጥ የከለላ አይነት ነው፡፡

ጥገኝነት ለማግኘት ማመልከት የሚችለው ማን ነው?

ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በአካል የሚገኙ ወይንም አስቀድሞ በተዘጋጀ የመድረሻ ስፍራ ላይ ሆነም አልሆነ ዩናይትድ ስቴትስ የደረሱ የዩናይትድ ስቴትስ ዜግነት የሌላቸው ሰዎች ማመልከት ይችላሉ፡፡

ጥገኝነት ለማግኘት ማመልከት ያለብኝ መቼ ነው?

በአጠቃላይ ጥገኝነት ለማግኘት ማመልከት ያለብዎ ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ በገቡ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ የሚከተሉትን የመሳሰሉ ልዩ ሁኔታዎች ተቀባይነት ሊኖራቸው ይችላል፡- (1) ለጥገኝነት ብቁ በመሆን እና ባለመሆንዎ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ በአናት ሀገርዎ ውስጥ የሚከሰቱ የሁኔታዎች መለዋወጥ ወይም (2) ዘግይተው ከማመልከትዎ ጋር ግንኙነት ያላቸው ከመደበኛው ወጣ ያሉ ሁኔታዎች፡፡

እዚህ ያለሁት በህገ ወጥ መንገድ ከሆነ ጥገኝነት ለማግኘት ማመልከት እችላለሁ?

አዎን፤ በደረሱ በአንድ አመት ውስጥ ማመልከቻዎን እስካስገቡ ድረስ ወይንም ከዚህ ህግ ውጭ ለመስተናገድ ብቁ መሆንዎን ማረጋገጥ እስከቻሉ ድረስ የስደተኝነት ሁኔታዎ ምንም ይሁን ምን ጥገኝነት ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ፡፡

በወንጀል ተፈርዶብኝ ከነበረ ማመልከት እችላለሁ?

አዎን፡፡ ነገር ግን እንደ ወንጀሉ አይነት ጥገኝነት ከማግኘት ሊታገዱ ይችላሉ፡፡

ጥገኝነት ለማግኘት ከማመልከት ወይንም ከማግኘት ልታገድ እችላለሁ?

ከዚህ በፊት ጥገኝነት ለማግኘት አመልክተው በስደተኞች ጉዳይ ዳኛ ወይንም በስደተኞች ጉዳይ ይግባኝ ሰሚ ቦርዱ ማመልከቻዎ ውድቅ የተደረገ ከሆነ፣ ለመጨረሻ ጊዜ በመጡ በአንድ አመት ውስጥ ካላመለከቱ ወይም በሁለትዮሽ ወይንም በብዙ ሀገራት መካከል በተደረገ ስምምነት መሠረት ደህንነቱ አስተማማኝ ወደሆነ ሦስተኛ ሀገር መወሰድ የሚችሉ ከሆነ ጥገኝነት ለማግኘት ከማመልከት ሊታገዱ ይችላሉ፡፡ በአንዳንድ የወንጀል ድርጊቶች የተነሳ፣ ከደህንነት ጋር የተያያዙ ምክንያቶች፣ ወይም በሌሎች ላይ ስቃይ እና እንግልት በማድረስ ተሳትፈው ከነበረ ወይም በሌላ ሀገር ውስጥ አስቀድመው ተደላድለው መልሰው የሰፈሩ ከሆነ ጥገኝነት ከማግኘት ሊታገዱ ይችላሉ፡፡ አንዳንድ ልዩ ሁኔታዎች ተቀባይነት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ነገር ግን ጥገኝነት ለማግኘት ከማመልከት የታገዱ ቢሆንም እንኳን መባረርን ማዘግየት ሊፈቀድልዎት የሚችል ሲሆን ይህም በመባረር እርምጃ ሂደቶች ውስጥ የሚሰጥ ሌላ በአንጻሩ ውስን የሆነ የከለላ አይነት ነው፡፡

ስለ ጥገኝነት አሰጣጥ ሂደት በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች

ተቀባይነት ያለው ጥገኝነት አጭር ምልከታ



አ.ኤ.አ. በ1883 በኤማ ላዛረስ ከተጻፈው "The New Colossu," ከተሰኘው መድብል የተቀነጨበ፡፡ ተስፋን ሰጪ የሆነው ይህ ግጥም በነህስ ላይ ተቀርጾ በነጻነት ሀውልቱ (Statute of Liberty) ማስቀመጫ የውስጥ ግድግዳ ላይ አ.ኤ.አ. በ190 ሰፍሯል፡፡

ጥገኝነት ለማግኘት የማመለክተው እንዴት ነው?
ጥገኝነት ለማግኘት ለማመልከት **የጥገኝነት እና መባረርን የማዘግያ ማመልከቻ** የሆነውን ቅጽ **I-589 (Form I-589 - *Application for Asylum and for Withholding of Removal*)** መሙላት እና መመሪያዎቹን በጥንቃቄ መከተል አለብዎት፡፡ ቅጾችን **http://www.uscis.gov/forms** በተሰኘው ድረ-ገጽ ላይ እንዲሁም በ**1-800-870-3676** የቅጽ መጠየቂያ መስመር ላይ በመደወል በነጻ ማግኘት ይቻላል፡፡

ጥገኝነት ለማግኘት ለማመልከት የሚከፈለው ክፍያ ምን ያህል ነው?
ጥገኝነት ለማግኘት ለማመልከት የሚከፈል ምንም ክፍያ የለም፡፡

ማመልከቻዬ ውስጥ ባለቤቴን እና ልጆቼን ማካተት እችላለሁ?
በሚያመለክቱበት ጊዜ ወይንም በማመልከቻዎ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ያሉ ባለቤትዎን እና ልጆችዎን ማካተት ይችላሉ፡፡ አንድ ልጅ በማመልከቻዎ ውስጥ ራሱን እንዳልቻለ ልጅ እንዲካተት ከ21 አመት በታች እና ያላገባ መሆን አለበት፡፡ በጥገኝነት ቃለ መጠይቅዎ ወቅት እንዲህ ያሉትን ራሳቸውን ያልቻሉ ልጆች ይዘው መምጣት አለብዎ፡፡

ለጥገኝነት ካመለከትኩ የደህንነት እና የኋለኛ ታሪክ ምርመራዎች ሊደረጉብኝ ይችላል?
አዎን፡፡ ጥገኝነት ለማግኘት የሚያመለክት እያንዳንዱ ሰው የኋለኛ ታሪክ እና የደህንነት ምርመራዎች ይደረጉበታል፡፡ ከእነዚህ ምርመራዎች በሚገኘው ውጤት መሠረት ጥገኝነት ለማግኘት ብቁ ያልሆኑ ሆነው ሊገኙ ይችላሉ፡፡

ለጥገኝነት ካመለከትኩ የጣት አሻራዬ ይወሰዳል?
አዎን፡፡ ጥገኝነት ለማግኘት ማመልከቻ ካስገቡ በኋላ በማመልከቻ ድጋፍ ማዕከል ውስጥ የጣት አሻራዎን የሚሰጡበትን ሠዓት፣ ቀን እና ስፍራ የሚገልጽ ደብዳቤ ይደርስዎታል፡፡

ለጥገኝነት ካመለከትኩ በኋላ ሥራ መሥራት እችላለሁ?
በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ ጥገኝነት ለማግኘት እና የሥራ ፍቃድ ለማግኘት ማመልከት አይችሉም፡፡ ነገር ግን በእርስዎ ምክንያት የተፈጠሩ መዘግየቶች ሳይቆጠሩ የጥገኝነት ማመልከቻዎን አሟልተው ካቀረቡ 150 ቀናት ካለፉ እና በማመልከቻው ላይ ምንም አይነት ውሳኔ ካልተሰጠ የሥራ ፍቃድ ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ጥገኝነት ከተሰጠዎ የጥገኝነት ማመልከቻዎ እንደጸደቀ ወዲያውኑ ስራ እንዲሰሩ ይፈቀድልዎታል፡፡

ለጥገኝነት ካመለከትኩኝ በኋላ ከዩናይትድ ስቴትስ ውጭ መጓዝ እችላለሁ?
በጥገኝነት ጉዳይዎ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት የግድ ከዩናይትድ ስቴትስ ውጭ መጓዝ ካለብዎ ዩናይትድ ስቴትስን ለቅቀው ከመውጣትዎ በፊት መመለስ እንዲችሉ አስቀድመው ፈቃድ ማግኘት ያለብዎ ሲሆን ይህም ፈቃድ በሌላ አጠራሩ አስቀድሞ የሚሰጥ የመውጫ ፈቃድ (Advance Parole) በመባል ይታወቃል፡፡ አስቀድመው የመውጫ ፈቃድ ሳያገኙ ከቀሩ USCIS ማመልከቻዎን ትተው እንደሄዱ አድርጎ የሚቆጥረው ሲሆን ወደ ዩናይትድ ስቴትስ መልሰው እንዳይገቡ ሊከለከሉ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም አስቀድመው የመውጫ ፍቃድ አግኝተው ስቃይ እና እንግልት ይደርስብኛል ብለው ወደሚሰጉበት ሀገር ተመልሰው ከሄዱ ተመልሰው ለመሄድዎ አሳማኝ የሆኑ ምክንያቶችን ካላቀረቡ በስተቀር USCIS የጥገኝነት ማመልከቻዎን እንዳነሱ አድርጎ ሊወስደው ይችላል፡፡

በጥገኝነት ቃለ-መጠይቄ ላይ ማን ሊረዳኝ ይችላል?
የዩናይትድ ስቴትስ መንግስትን ምንም ወጪ ሳያስወጡ ለጥገኝነት ቃለ-መጠይቅ ሲመጡ የራስዎን የህግ አማካሪ ወይንም ተወካይ ይዘው መምጣት ይችላሉ፡፡

እንግሊዝኛ የማልናገር ከሆነ ቃለ-መጠይቅ የሚደረግልኝ እንዴት ነው?
በአስተርጓሚ አማካኝነት ቃለ-መጠይቅ ይደረግልዎታል፡፡ USCIS አስተርጓሚዎችን አያቀርብም፡፡ የራስዎን አስተርጓሚ ይዘው ወደ ቃለ መጠይቁ መምጣት አለብዎ፡፡ አስተርጓሚዎ በቂ በሆነ መልኩ እንግሊዝኛ የማይናገር ከሆነ የተሻለ ብቃት ያለው አስተርጓሚ ማግኘት እንዲችሉ ሲባል ቃለ-መጠይቅዎን ወደ ሌላ ቀን ማዛወር ሊያስፈልግ ይችላል፡፡

በጥገኝነት ቃለ-መጠይቄ ላይ ምን ይደረጋል?
ከጥገኝነት ሠራተኛው ጋር ክርክር የሌለበት ቃለ-መጠይቅ ለማድረግ ወደ ጥገኝነት ቢሮው ይመጣሉ፤ ሠራተኛው ማንነትዎን ካረጋገጠ በኋላ መሠረታዊ የሆኑ ከግል ታሪክዎ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን እና ጥገኝነት ለማግኘት የፈለጉባቸውን ምክንያቶች ይጠይቅዎታል፡፡ በቃለ-መጠይቁ ላይ የሚናገሩት ነገር ሁሉ ምስጥራዊነቱ የተጠበቀ ነው፡፡ የጥገኝነት ሠራተኛው ስደተኛ ለመባል ብቁ መሆንዎን ለመወሰን እንዲችል ያሳለፉትን ተሞክሮ በተቻለ መጠን ዘርዝረው ለጥገኝነት ሠራተኛው መንገር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የጥገኝነት ቃለ-መጠይቁ በተደረገበት በተመሳሳይ ቀን በማመልከቻዎ ላይ ውሳኔ አይሰጥም፡፡

የጥገኝነት ሠራተኛው ጥገኝነት ለማግኘት ብቁ መሆኔን የሚወስነው በምን መልኩ ነው?
የጥገኝነት ሠራተኛው ብቁ መሆንዎን የሚወስነው በማመልከቻዎ ላይ እና ከጥገኝነት ሠራተኛው ጋር ባደረጉት ቃለ-መጠይቅ ላይ ያቀረቧቸውን መረጃዎች እንዲሁም ሠራተኛው ማግኘት የሚችላቸውን ሌሎች መረጃዎች መሠረት በማድረግ የስደተኛ ትርጓሜን የሚያሟሉ መሆኑን በመመዘን ነው፡፡

ጥገኝነት ለማግኘት ብቁ ሳልሆን ብገኝ ምን ይፈጠራል?
ለጥገኝነት ብቁ አይደሉም ተብሎ ተወስኖ ነገር ግን የስደተኝነት ሁኔታዎ ተቀባይነት ያለው ከሆነ ወይም (በጊዜያዊ ከለላ ወይንም አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በአመክሮ አማካኝነት) ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ለመቆየት መስፈርቱን የሚያሟሉ ከሆነ ብቁ አይደሉም ተብሎ የተወሰነበትን ምክንያት የሚያስረዳ ጉዳይዎ ውድቅ መደረጉን የሚገልጽ ደብዳቤ ይደርስዎታል፡፡ እነዚህን ምክንያቶች ውድቅ ለማስደረግ እና ጉዳይዎን ለማጠናከር ተጨማሪ ማስረጃዎችን ለማቅረብ እድል ይኖርዎታል፡፡ ተቀባይነት ያለው የስደተኝነት ሁኔታ ያለዎት ካልሆነ ወይም ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ለመቆየት መስፈርቱን የማያሟሉ ከሆነ የመባረር የፍርድ ሂደት ውስጥ እንዲገቡ የሚደረግ ሲሆን የጥገኝነት ጉዳይዎን እንደ አዲስ የሚያይ የስደተኛ ጉዳዮች ዳኛ ጋር ይላካሉ፡፡

ጉዳዬ የሚገኝበትን ሁኔታ ማወቅ የምችለው እንዴት ነው?
እባክዎ የጥገኝነት ቃለ-መጠይቅዎን ያከናወነውን ወይንም የሚያከናውነውን የUSCIS የጥገኝነት ቢሮ ያነጋግሩ፡፡

ህጉን የት ማግኘት እችላለሁ?
የጥገኝነት የህግ መሠረት የሚገኘው የስደተኛ እና ዜግነት ህጉ (INA) አንቀጽ 208 ውስጥ ነው፡፡ ለጥገኝነት ብቁ የመሆን መስፈርቶችን እና አሠራሮችን የሚዘረዝሩት የፌዴራል መመሪያዎችን በፌዴራል መመሪያዎች ህግ (CFR) ቁጥር 8 አንቀጽ 208 ውስጥ ማግኘት ይቻላል፡፡

የመጀመሪያ እርምጃ፡- ጥገኝነት ፈላጊው ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ይመጣል
አንድ ጥገኝነት ፈላጊ በአጠቃላይ ጥገኝነት ለማግኘት ለማመልከት በስደተኛ እና ዜግነት ህጉ (INA) አንቀጽ 208(a) መሠረት ብቁ የሚሆነው 1) ወደ ዩናይትድ ስቴትስ እየገባ ከሆነ ወይም ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በአካል የሚገኝ ከሆነ እና 2) ወደ ዩናይትድ ስቴትስ በመጣ በአንድ አመት ውስጥ ካመለከተ ወይም በአንድ አመት ውስጥ ማመልከትን በሚጠይቀው ህግ ውስጥ የተቀመጡት ልዩ ሁኔታዎች የሚመለከቱት መሆኑን ማረጋገጥ የሚችል ከሆነ ነው፡፡

ሁለተኛ እርምጃ፡- ጥገኝነት ፈላጊው ጥገኝነት ለማግኘት ያመለክታል
ጥገኝነት ፈላጊው **የጥገኝነት እና መባረርን የማቆያ ማመልከቻ** የሆነውን ቅጽ **I-589** አግባብ ላለው አገልግሎት መስጫ ማዕከል ያስገባል፡፡

ሶስተኛ እርምጃ፡- አመልካቹ የጣት አሻራው ይወሰዳል እንዲሁም የኋለኛ ታሪክ የደህንነት ምርመራዎች ይከናወናሉ
እድሜያቸው ከ13 አመት በላይ የሆነ አመልካቾች ወደ አንድ የአመልካቾች ድጋፍ መስጫ ማእከል ወይንም ስልጣኑ ወዳለው ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀ የህግ አስፈጻሚ ኤጀንሲ ጋር በመቅረብ የጣት አሻራቸውን እንዲሰጡ ማሳሰቢያ ይደርሳቸዋል፡፡

አራተኛ እርምጃ፡- አመልካቹ ቃለ-መጠይቁን የሚመለከት ማሳሰቢያ ይደርሰዋል
አብዛኛውን ጊዜ አመልካቹ ቅጽ I-589ን ሞልቶ ባስገባ በ21 ቀናት ውስጥ የጥገኝነት ቃለ-መጠይቁ የሚከናወንበትን ቀን፣ ስፍራ እና ሠዓት የሚገልጽ ማሳሰቢያ ይደርሰዋል፡፡

አምስተኛ እርምጃ፡- አመልካቹ ቃለ-መጠይቅ ይደረግለታል
አመልካቹ በአርሊንግተን፣ ቨርጂኒያ፤ ቺካጎ፣ ኢለኖይ፤ ሂዩስተን፣ ቴክሳስ፤ ሎስ አንጀለስ፣ ካሊፎርኒያ፤ ማያሚ፣ ፍሎሪዳ፤ ኒዋርክ (ሊንደርስት)፣ ኒው ጀርሲ፤ ኒው ዮርክ (ሮዝዴል)፣ ኒው ዮርክ፤ እና ሳን ፍራንሲስኮ፤ ካሊፎርኒያ ከሚገኙት ስምንት የጥገኝነት ቢሮዎች ውስጥ ወይንም ደግሞ አመልካቹ የሚኖረው ከጥገኝነት ቢሮው በጣም ርቆ ከሆነ ደግሞ በዲስትሪክቱ ቢሮ የጥገኝነት ሠራተኛ አማካኝነት ቃለ-መጠይቅ ይደረግለታል፡፡ የጥገኝነት ሠራተኞቹ ወደ ቢሮዎቹ ለመጓዝ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ስለሚኖርባቸው በዲስትሪክቱ ቢሮ ቃለ-መጠይቅ ለሚደረግላቸው አመልካቾች የሚወስደው ጊዜ ረዘም ያለ ሊሆን ቢችልም አብዛኛውን ጊዜ አመልካቹ ባመለከተ በ43 ቀናት ውስጥ ቃለ-መጠይቅ ይደረግለታል፡፡